# ኢየሱስ ክርስቶስን እንከተላለን

ካህን ክውንተን ኤል ኩክ
የአስራ ሑለት ሐዋሪታይ ቡድን አባል

እህት Lant እና ለአማካሪዎቿ ለሰጡት አስደናቂ አገልግሎት ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በአለም ውስጥ ጌታችንን እና አዳኛችንን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚወዱት የኋለኛው ቀን ቅዱሳን በትንሳኤ ሰንበት ለመናገር ያለኝ ሀላፊነት ታላቅ ነው። በዚህ ጠዋት በሞት ላይ ያለውን ድል እናከብራለን። በገትሰመኔ እና በካልቨሪ ላደረገው ተስዋኦ ያለንን እውቀት እና በልባችን የሚሰማንን ዋጋ እንሰጠዋለን። ለአባቱ ፍላጎት ፈቃደኛ በመሆን በሞት ላይ ድልን አገኘ እና ከሰው ዘር ታሪክ በላይም አስደናቂ ሆነ። አዳኝን ስለመከተል ለመናገር ላለኝ እድል ምስጋና አለኝ።

በካልቨሪ ከመሞቱ በፊት የነበረው የአዳኝ ስጋዊ አገልግሎት የመጨረሻ ሁለት ቀናት ታላቅ ትርጉም ያላቸው እና በአንዳንድም ለመግባት የሚያስቸግሩ ናቸው። ለዘለአለም እጣ ፈንታችን አስፈላጊ የሆኑት በሀሙስ እና ክርስቶስ በተሰቀለበት አርብ ነበር። የመጨረሻው እራት የተጀመረው "እስራኤል ከባሪያነት የተለቀቁበትን ቀን በሚያከብሩበት" በፋሲካ በሀሙስ ምሽት ውስጥ ነበር። በዚህ የመጨረሻ እራት ላይ ታላቅ ትርጉም ያላቸው ስነ ስርዓቶች እና ትምህርቶች ተጀምረው ነበር። ሶስትን ብቻ እጠቅሳለሁ። መጀመሪያ፣ አዳኝ የቅዱስ ቁርባንን ስነስርዓት አስተዋወቀ። ዳቦ ወሰደ፣ እና ጸለየ፣ እናም ወደ ደቀመዛሙርቱም እንዲህ በማለት ቆርሶ ሰጣቸው፣ "ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት።"3 እንደዚህም ቅዱስ ቁርባንን አስተዋወቀ። ሁለተኛ፣ በትኩረት ያስተማረው ፍቅርን እንደ ዋና መሰረታዊ መመሪያ ነው። እንዲህም አስተማረ፣ "እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።"4 ሶስተኛ፣ በክርስቶስ መማለድ ወይም አመራር በኩል "መንፈስ ቅዱስ እንደ ሌላ አፅናኚ ለሐዋሪያት ቃል ተገብቶ ነበር።"

አዳኝ የኃጥያት ክፍያውን ፈጸመ። በእራሱም ላይ "የሰው ዘር ኀጥያትን ሸክም" እና ሰይጣን ሊያመጣበት የሚችለውን ክፋት" ወሰደ። በዚህም መንገድ ውሸተኛውን ክስ እና ወደ መሰቀሉ የመሩትን አሳዛኝ ሁኔታዎችን ተፅናና። ይህም በመጨረሻ በክርስቶስ ከሞት በትንሳኤ ሰንበት በመነሳት ተፈጸመ። ክርስቶስ እንደ አዳኝ እና ቤዛ የነበረው ቅዱስ ሚስዮንን አሟላ። ከሞት እና ከሲኦል አዳነን። ከሞት በመነሳት መንፈሶቻችን ከሰውነቶቻችን ጋር እንደገና ይገናኛሉ። በግል ብቁነት በኩል በጸጋው ወደ እግዚአብሔር ፊት ተመልሰን የመግባት ግርማዊ እድል ይኖረናል።

በትንሳኤ ሰንበት ከ11ዱ ነብያት በተጨማሪ ለብዙዎች ከሞት የተነሳው አዳኝ ታዩ። ከሞት የተነሳውን ጌታ ሲያዩ ይሰማቸው የነበረውን ከሁሉም በላይ ደስታ አስቡበት።

ነብዩ ጆሴፍ ስሚዝ ስለትንሳኤ ሲናገርባቸው እንዲህ አለ፤

የሀይማኖታችን መሰረታዊ መመሪያዎች ክርስቶስን በሚመለከተ፣ እንደሞተ፣ እና እንደገናም በሶስተኛው ቀን እንደተነሳ፣ እና ወደሰማይ እንዳረገ በሰጡን በሐዋሪያት እና በነብያት ምስክር ነበር፤ ስለሀይማኖታችን የሚመለከቱት ሌሎች ነገሮች ሁሉ ለዚህ ተጣባቂዎች ናቸው።

በገትሰመኒ እና በካልቨሪ ታላቅ ትርጉም ብንደሰትም፣ ሁልጊዜም የምናተኩረው ከሞት በተነሳው ጌታ ላይ ነው። የጥንት የክርስቲያን ቤተክርስትያን አማኞች አድኝን "…ከሞት እንደተነሳ፣ ዘለአለማዊ፣ ግርማዊ ክርስቶስ" እና ያሰቡበትም በቀስቅል ላይ እያለ ሳይሆን በዙፋን ላይ እንዳለ…" እንደሚያከብሩት Frederic Farrar መስክሯል።

ለአለም የምናቀርበው ምልእክታችን እርሱ ህያው እንደሆነ ነው ብለው ፕሬዘደንት ሒንክሊ አስተምረዋል። ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን የክርስቶስ ምልክት የሚገኘው እምነታችንን በምንገልፅበት እና ወንጌልን በምንኖርበት ውስጥ ነው።18

ዛሬ ክርስትያን መሆን ምን እንደሆነ ስናስብበት፣ የደቀ መዛሙርትነታችን መንገድ ምን እንደሚጥይቅብን አስቡ። በስጋዊ ህይወቱ መጨረሻው ሁለት ቀናት ያደረገውን እንድናስብባቸው እና በትክክለኛም መንገድ እንድንከተላቸው ሀሳብ አቀርባለሁ።

መጀመሪያ፣ አዳኝ ቅዱስ ቁርባንን ያስተዋወቀበትን አስቡበት። አዳኝ ምን እንደሚደርስበት አውቆ ነበር። በቅድመ ምድራዊ በሰማይ ጦርነት የተጀመረው ቅዱስ የኋጥያት ክፍያ ሚስዮኑ በዚያ ምሽት እና በሚቀጥለው ቀን ሊጀመሩ ነበር። ምንም እንኳን በጠላቶጩ ለፍርድ የሚቀርብበት በፊት እየመጣ ቢሆንም፣ በውሸተኛ ከሳሾቹ ጋር የሚከራከርበትን እንደሚያዘጋጅ የሚታይበት አልነበረም። አዳኝ ከዚህ ምትክ የቅዱስ ቁርባን ቅዱስ ስነስርዓትን ለደቀ መዛሙርቱ አስተዋወቀ። ስለዚያ ቅዱስ ድርጊት በማሰላሰልበት ጊዜ ስሜታዎቹ በዝልቅ ይነካሉ።፡በቤተክርስትያና ውስጥ የቅዱስ ቁርባን ስብሰባ ከሌሎቹ ስብሰባዎች ሁሉ የተቀደሰ እና ቅዱስ የሆነ ስብሰባ ነው። ከሞት ከተነሳም በኋላ፣ አዳኝ ቅዱስ ቁርባንን ከኔፋውያን መካከል ጀመረ። የእርሱ ደቀ መዛሙርት እና የእርሱ ቤተክርስትያን እውነተኛ አባሎች ከሆንን፣ ቅዱስ ቁርባንን ማስታወስ እና ማክበር አለብን። በተሰበረ ልብ እና በተጸጸተ መንፈስ አዳኝን ለመከተል፣ ንስሀ ለመግባት እና በክርስቶስ ሄጥያት ክፍያ በኩል ቅድሳን ለመሆን ያለንን ፈቃደኝነት እያንዳንዳችን እንድንገል ይፈቅድልናል።20 ቅዱስ ቁርባንም ለእግዚአብሔር ልጁን እንደምናስታውስ እና የጥምቀት ቃል ኪዳናችንን ስናሳድስ ትእዛዛቱን እንደምናከብር እንድንመሰክርለት እፈቅድልናል። ይህም ለአብና ለወልድ ያለንን ፍቅራችንን ያሳድገዋል።

አዳኝ በፍቅር እና አንድነት ላይ አተኩሯል እና እርስ በራስ ከተዋደድን እንደእርሱ ደቀ መዛሙርት እንደምንታወቅ ገልጿል። ዘለአለማዊ ውጤታ ያለውን የኃጥያት ክፍያ ስናስብበት፣ ይህ አይነት ትእዛዝ ታዛዥ የመሆን ጥረታችን ያስፈልገዋል። ፍትእዛዛቱን ስናከብር እና ልጆቹን ስናገለግል ፍቅራችንን እንገልጻለን። የሄጥያት ክፍያን በሙሉ ሊገባን አንችልም፣ ነገር ግን ህይወታችንን ምንም ፈተና ቢመጣብንም አፍቃሪ እና ደግ በመሆን ለማሳለፍ እንችላለን። በዚህ መንገድ የክርስቶስ አይነት ለመሆን እንችላለን።

ለደቀመዛሙርቱ ክርስቶስ የሰጠው ሀላፊነት እርስ በእራስ እንዲዋደዱ ነው እና ይህን መሰረታዊ መመሪያ በመጨረሻው እራት ጊዜ ያስተማረበትም ከስጋዊ ህይወቱ መጨረሻ ቀናት ላይ ከነበሩት ድርጊቶች በላይ በጣም ስሜትን የሚነካ እና አስደሳች ድርጊት ነው።

የስነ ምግባር ጻባይ ክፍል ትምህርትን ብቻ የሚያስተምር አልነበረም። ይህም የእግዚአብሔር ልጅ ሐዋሪያቱን እና ከእነርሱ በኋላ የሚመጡትን ደቀ መዛሙርቱን ይህን ዋና ትምህርትይን እንዲያስታውሱ እና እንዲከተሉ  የለመነበት ነው። እርስ በራስ የምንገናኝበት እና የምንደራረግበት ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል እንዴት ፈቃደኛ እንደሆንን የምንመዝንበት ነው።

የዚህን ጉባኤ መልእክት ስናዳምጥ ልቦቻችን ይነካሉ እና የተሻለ ለማድረግም ውሳኔ እናደርጋለን። ነገር ግን በሰኞ በብዙ ጊዜ በሁከታ ላይ ወዳለው ስራ፣ ት/ቤት፣ እና ወደ አለም እንመለሳለን። በዚህ አለም ብዙዎች እርስ በርስ የተፈራሩ እና የተናደዱ ናቸው። እነዚህ ስሜታዎች የሚገቡን ብንሆንም፣ በንግግራችን እና ከሰዎች ጋር ባሉን ግንኙቶች አክባሪ መሆን ይገባናል። ይህም በልዩ በማንግባባበት ጊዜ እውነት መሆን ይገባዋል። አዳኝ ጠላታችንንም ቢሆን እንድንወድ አስተምሮናል። ብዙዎቹ አባሎቻችን ይህን ምክር ያዳምጣሉ። አንዳንዶች ግን ንዴታቸውን ወይም አስተያየታቸውን በቁጣ ማሳየት ክርስቶስ እንደኖረው እና እንዳስተማረው ከማድረግ በላይ አስፈላጊ የሆነ የሚመስላቸው ናቸው: በማንስማማበት ጊዜ የምናደርገው  እና አዳኝን በእውነት እንደምንከተል የምንመዘንበት እንደሆነ እንድናውቅ እያንዳንዳችንን እጋብዛለሁ።  አለመስማማት አንዳንዴ አስፈላጊ እንደሆነ፣ ግን የማይስማማ መሆን ግን መጥፎ አይደለም። ሁከታ እና ነገሮችን ማጥፋት የአለመስማማት መልሶች አይደሉም። በችግር ጊዜም ቢሆን ፍቅርን እና ክብርን ካሳየን፣ እንደክርስቶስ አይነት በተጨማሪም እንሆናለን።

አዳኝ ለአስራሁለቱ መንፈስ ቅዱስን ለመስጠት ቃል መግባቱ በሰማይ አባታችን አላማ ውስጥ መንፈስ ቅዱስን ያለውን ታላቅ ሀላፊነት መሰረተ። መንፈስ ቅዱስ የመንፈስ ሰው ነው እና ስለአብ እና ወልድ የሚመሰክር፣ ስለሁሉም ነገሮች እውነትን የሚገልጽ፣ ንስሀ የገቡትንና የተጠመቁትን የሚቀድስ አፅናኚ ነው። የቃል ኪዳን ቅዱስ መንፈስ ተብሎም ይጠራል፣ እና እንደዚህም የእያንዳንዳችንን ጻድቃዊ ስራዎችን፣ ስነ ስርዓቶችን፣ እና ቃል ኪዳኖችን ያረጋግጣል። በቅዱስ ቃል ኪዳን መንፈስ መታተምን ያገኙትም አብ ያለውን ሁሉ ይወርሳሉ።

በማንኛውም ጊዜ ምንም ትርጉም የሌለውን ነገሮች ለማዳመጥ እና ለማየት በምንችልበት ጩኸት በተሞላበት አለም ውስጥ እንኖራለን። በመንፈስ ቅዱስ ለመነሳሳት ከፈለግን፣ ቀስ ለማለት፣ ለማሰላሰል፣ ለመጸለይ፣ እና የእርሱን መነሳሻ ለመቀበል እና ለመከተል ብቁ በመሆን ለመኖር ጊዜን ማግኘት ይገባናል። እንደ አባላት ከእርሱ ብርሀን እና እውቀትን የመቀበል እድል አለን።

በገትሰመኒ እና በካልቨሪ አዳኝ የተጋጠማቸው የኃጥያት ክፍያ ፈተናዎች ለእኛ ታላቅ ምሳሌዎች ናቸው። ሊገባን የማይችሉ የአዕምሮ፣ የሰውነት እና የመንፈስ ስቃይ አጋጠመው። በገትሰመኔ ወደ አባቱ እንዲህ ሲል ጸለየ፣ “አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን” በማለት እንዲጸልይ አስደረገው። እንደእርሱ ደቀመዛሙርት፣ ታላቅ ባይሆኑም የአዕምሮ፣ የሰውነት እና የመንፈስ ስቃይ ያጋጥመናል። ለብዙዎቻችን የምንሞከርበት እና ያለምክንያት የምንሰቃይበት እና የምንሳቀበትና ልንሸከማቸው የማንችላቸው የሚመስሉን ስጋዊና

መንፈሳዊ ችግሮች የሚያመጡብን፣ እና መራራዋ ፅዋ ከእኛ እንድታልፍ የምንጸልይበት ጊዜ ይኖራል። ማንም ከህይወት ችግር ነጻ የሆነ አይደለም።

ለአዳኝ ዳግም ምፅአት እየተዘጋጀን ነን። ማንም ሰው ይህ መቼ እንደሆነ እንዳማያውቁ ቅዱስ መጻህፍት ግልፅ ናቸው። ቅዱስ መጻህፍትም "…ምድር መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል"22 እና "…ከገደባቸው በላይ እራሳቸውን የሚወረውሩ የባህር ማዕበል…"23 በመጨረሻው ቀናት እንደሚኖሩም ቅዱስ መሳህፍት ነግረውናል።

እነዚህም ከቺሌ፣ ከሄቲ፣ እና ከፓቺፊች ደሴቶች በተጨማሪ በተላያዩ ቦታዎች ደርሰዋል። ከትንሽ ሳምንት በፊት ኤጲስ ቆጶስ H. David Burton, እና Tad R. Callisterና እኔ ባለፈው መስከረም በባህር ንፋስ ምክንያት በሳሞአ ቤተሰቦቻቸው ከሞቱባቸው ሰዎች ጋር ተገናኝተን ነበር። ቤተክርስትያኑ ሙሉ ነበር እና ስሜታዊ ስብሰባ ነበር። እነዚህን ብቁ አባላት በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጥያት ክፍያ ምክንያት ከሞቱባቸው ከሚያፈቅሯቸው ጋር እንደገና ለመገናኘት እንደሚችሉ አረጋግጥንላቸው።

የስቴክ ፕሬዘደንቱ Sonny Purcell ውሀው ከባህሩ ሲመጣ ያዩት መከናቸውን እየነዱ እያሉ ነበር። ወደትምህርት ቤት ለመሄድ በመንገድ ላይ ያሉትን ልጆች ክላክሳቸውን በመንፋት ወደከፍተኛ ቦታ እና ወደ ደህናነት ወዲያው እንዲሮጡ አስጠነቀቋቸው። ልጆቹም የነገሯቸውን አደረጉ። ቶሎ ብለው የ4 አመት ልጃቸውን አንስተው እናታቸውን ለማኘንት ለመሞከር ሄዱ። ከመድረሱ በፊት ውሀው መኪናቸውን 90 ሜትር ወደላይ አንስቶት በዛፍ ላይ አሳረፈው። ሴት ልጁን በመኪናው ጣራ ላይ አስቀመጣት እና ከቤታቸው አጠገብ በዛፍ ላይ ተንጠንጥላ የነበረቸውን እናቱን ለማዳን ይዋኝ ጀመር። ከጥረት ወደ መኪናው ከእርሷ ጋር ወደመኪናው ዋኘ። ብዚዎች እንደዚህ እድለኛ አልነበሩም። ወደከፍተኛ ቦታ እና ወደ ደህናነት ለመሄድ ጊዜ አልነበራቸውም። ብዙዎች፣ በልዩም ትትንሽ ልጆች እና ሽማግሌዎች ሞቱ።

ለሳሞአ ቤተሰቦችም በአለም ውስጥ የሚገኙት አባላት ፍቅራቸውን እና ሀሳባቸውን እንዳቀረቡላቸው፣ እንደጸለዩላቸው እና ገንዘብም ለእነርሱ እና ለጎረቤቶቻቸው እርዳታ እንደሰጡ ነገርናቸው። በሄቲ እና በቺሌ ላሉት አባላት እና ጎረቤቶቻቸው ይህም እውነት ነው። ይህንም የምናደርገው ኢየሱስ ክርስቶስን ስለምንከተል ነው።

ከሳሞአ ቤተሰቦች ጋር ስንገናኝ፣ ወደ መንፈሳዊ ከፍተኛ ቦታ ለሚሻል ህይወት የመሄድ እና የሚያድኑ ስነስርአቶች በጥብቅ የመያዝ አስፈላጊነት ግልጽ ነው። የአዳኝ ምሳሌ እና ህይወት የአለም ጉዳዮች የሚገኙበትን ያታችኛውን መንከስ እንድናስወገድ ያስተምረናል። ከስብሰባው በኋላ ከአባላት ጋር እጅ ስንጨባበጥ፣ አንድ እህት ሴት ልጇ እንደሞተች እና ወደቤተመቅደስ ከና እንዳልሄዱ ነገረችኝ። አሁን ዋና አላማቸው ለዘለአለም አብረው እንዲሆኑ ለቤተመቅደስ ስነስርዓቶች ለመዘጋጀት ነው አለች።

ይህች እህት ያለችውን እና የአለም የአሁንን ጉዳይ ሳሰላስል፣ ከፍተኛ ቦታ የሆነውን፣ መሰሰጃ እና ዘለአለማዊ መጠበቂያ የሆነውን ቤተመቅደስ እንድትፈልጉ ጥብቅ ምክር እንድሰጣችሁ ተሰማኝ።

በትንሳኤ ሰንበት በሚያዝያ 3 ቀን 1836 ዓ/ም፣ የከርትላንድ ቤተመቅደስ ከተቀደሰበት አንድ ሳምንት በኋላ፣ አስራ ሑለቱ የጌታን ቅዱስ ቁርባን ለአባላት በማካፈል ተሳተፉ። ከስብሰባው የረጋና ጸጥተኛ

ጸሎት በኋላ፣ አዳኝ ለነብዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ለኦሊቨር ካውደሪ በግርማው ታየ እና በሞሴ እና ኤልያስ በኩልም ቤተሰቦችን ለዘለአለም የሚያስተሳስር ቅዱስ የመተሳሰሪያ ሀይል አይነት ተጨማሪ የክህነት ስልጣን ቁልፎችን ዳግመው ተመለሱ።24

ዛሬ በዚህ የትንሳኤ ሰንበት ጠዋት አዳኝ ያደረገልንን ነገሮች ሁሉ እንደሰትባቸዋለን። ሁላችንም ደህንነት እና ዘለአለማዊነት እንድናገኝ አድርጓል። ነገር ግን እንደ ሳሞአ ልጆች፣ ለሰላም እና ለደህናነት ወደአዘጋጀልን ከፍተኛ ቦታዎች በፍጥነት መሮጥ አለብን።

ይህን የምናደርግበት አንዱ መንገድ ቢኖር የህያው ነቢያችን ፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ ሞንሰን የሚያስተምሩትን በጥብቅ በመከተል ነው። ስለህያው ነቢያትም ጌታ እንዲህ አለ፣ "ቃሉን ልክ ከእኔ አፍ እንደወጣ አድርጋችሁ በሙሉ ትግስት እና እምነት ትቀበላላችሁ።"25 ፕሬዘደንት ሞንሰን አዳኝን በመከተል ጥሩ ምሳሌ ናቸው።

በዚህ በግርማዊ የትንሳኤ ጠዋት በ Eliza R. Snow ከተጻፈው ከሚለው መዝሙር ቅላት የተኦላሁ ነኝ።

"እንዴት ታላቅ፣ ግርማዊ እና ፍጹም፣
የቤዛነት ታላቅ አላማ፣
ፍትሀ፣ ፍቅርና ምህረት የሚገናኙበት
በመለኮታዊ መዋሀድ!"

ኢየሱስ ክርስቶስ ህያው እንደሆ፣ የአለም አዳኝ እና ቤዛ እንደሆነ የሐዋሪያትነት ምስክሬን እሰጣለሁ። ለእውነተኛ ደስታ መንገድም አዘጋጅቷል። ስለዚህ የምመሰክረው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፣ አሜን።